204 J-P.R.S -

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1993 በጀት ዓመት
# የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1993

በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1993 በጀት ዓመት
# የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1993

## ማ ው ጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ | 2 |
| 2.1 የሥነ-ሕዝብና ጤና (DHS) በተመለከተ | 2 |
| 2.2 የ1996 ዓ.ም አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅትን በተመለከተ | 3 |
| 2.3 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ | 4 |
| 2.4 የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓትና የሕዝብ ምዝገባን በተመለከተ | 4 |
| 2.5 የሰው ኃይል ስታቲስቲክስን በተመለከተ | 5 |
| 2.6 ማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ | 6 |
| 2.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት | 7 |
| 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ | 8 |
| 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት | 8 |
| 3.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት | 12 |
| 3.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት | 16 |
| 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ | 20 |
| 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ | 20 |
| 4.2 የካርቶግራፊ ሥራን በተመለከተ | 23 |
| 4.3 የመዛግብት አያያዝና ስታንዳርድስ በተመለከተ | 24 |
| 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ | 25 |
| 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና | 26 |
| 6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ | 26 |
| 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ | 27 |
| 7. የበጀት አጠቃቀም | 29 |
| ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም | 30 |
| ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም | 31 |
| 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት | 32 |
| 8.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች | 33 |
| 8.2 ትራንስፖርትና ጥገናን በተመለከተ | 33 |
| 8.3 ሕትመት | 34 |
| 8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ | 34 |
| 9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች | 36 |

# የ1993 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የአገሪቱን ስታቲስቲካዊ መረጃ ፍላጎት ለማሟላት ባለፉት ዓመታት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ሕዝብ ጥናቶችን ያካሄደ ሲሆን፣ አሁንም በማከናወን ላይ ይገኛል። የባለሥልጣን መ/ቤቱ ከመንግሥት በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ በየዓመቱ የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥራ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠርና በየጊዜው አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የአገሪቱን የመረጃ ሃብት አለም አቀፋዊ ይዘትና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

በ1993 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት በተመደበ የካፒታል በጀት ሰባት ልዩ ልዩ ጥናቶችንና በ1994 ዓ.ም ለሚካሄደው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያገለግል የሙከራ ጥናትና የግብርና ቆጠራውን ለማስፈፀም ሌሎች የዝግጅት ሥራዎችን ያካሄደ ሲሆን፣ በ1992 በጀት ዓመት ለተካሄዱ ስድስት የተለያዩ ጥናቶች የሪፖርት ዝግጅታቸውን ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር። እነዚህ ጥናቶችም፦

### ሀ. <u>በ1993 በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ሲካሄዱ የነበሩ ጥናቶች</u>

- I. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- II. የግብርና ናሙና ጥናት፣ ( የመኸርና የበልግ ወቅት፣ የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ጥናት)፣
- III. የመንግሥትና የግል ንግድ እርሻዎች ጥናት፣
- IV. የመካከለኛ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- V. የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- VI. የዕቃዎችና አገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- VII. የሕፃናት የሥራ ሁኔታ ( Stand - alone Child Labour ) ጥናት፣

ለ. <u>የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት</u>

ሐ. <u>በ1992 ዓ.ም. የተጀመሩና በዕቅድ ዓመቱ የሚጠናቀቁ የጥናት ሪፖርቶች</u>

I. የ1992 የግብርና ናሙና የበልግ ወቅት ጥናት፣
II. የዲሞግራፊና ጤና ጥናት (DHS)
III. የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት፣
IV. የ1992 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
V. የ1992 የኮንስትራክሽን ጥናት፣
VI. የ1992 የማዕድን ቁፋሮ ጥናት ናቸው።

በመሆኑም በ1993 በጀት ዓመት ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች ለማከናወን የተደረገውን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በዝርዝር በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተተ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራትም ተጠቃለው ቀርበዋል። እንደዚሁም ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት ውስጥ በዕቅድ አፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች፣ በመ/ቤቱ የተሰጡ መፍትሄዎችና የበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 2. <u>የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ</u>

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በየዘርፉ ያለውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲሁም አስተማማኝና ተከታታይነቱን የጠበቀ መረጃ እንዲኖር ለማድረግ ሕዝብ ነክ ጥናቶችን በማካሄድ ውጤቱን በየጊዜው ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል። በተመሣሣይ ሁኔታ በ1993 በጀት ዓመት የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል።

### 2.1 <u>የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናትን (DHS) በተመለከተ</u>

- በ1992 በጀት ዓመት በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት (DHS) ዋና ዋናዎቹ መረጃዎች የሚይዝ አጭር የቅድሚያ ሪፖርት (Preliminary Report) ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች የማማሸ ቀን የመረጃ ስርጭት ሴሚናር በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወር ላይ ተካሂዷል። በዕለቱም የሪፖርቱ ኮፒ ከመታደሉም በላይ የተለያዩ ጽሑፎችም በባለሙያዎች ቀርበዋል። በሴሚናሩ ላይም

ከመንግሥታዊ መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከምርምር ተቋማትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡ የጥናቱም ውጤት ከሁሉም አቅጣጫዎች ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

- የሥነ- ሕዝብና ጤና ጥናት መረጃ ዋናው ሪፓርት ዝግጅት ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ ለሪፖርቱ ዝግጅት የሚያስፈልጉ የኮምፒዩተር ሠንጠረዦችን ማውጣትና አጠቃላይ የሪፖርት ዝግጅቱ ከ MACRO INTERNATIONAL ጋር በመተባበር ተከናውኗል፡፡ ሪፖርቱ ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዲኖረው ሦስት የመ/ቤቱ ባለሙያዎች አሜሪካን በሚገኘው የMACRO INTERNATIONAL ድርጅት ዋና መ/ቤት በመሄድ ከድርጅቱ ባለሙያ አቻዎቻቸው ጋር በመሆን ሪፖርቱን አሻሽለውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች የተቋቋመው የማኔጅመንት ኮሚቴ ( ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን፣ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት፣ USAID እና UNFPA ) ድራፍት ሪፖርቱን ተመልክተውና አስተያየት ሰጥተውበት እርማቶቹ ላይ ከ MACRO INTERNATIONAL ጋር ውይይት ተካሂዶባቸው ሪፖርቱ የመጨረሻ መልኩን እንዲይዝ ተደርጎ ታትሟል፡፡
- የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት ዋና ሪፖርትን በተመለከተ ለመረጃ ተጠቃሚዎች የአንድ ቀን የመረጃ ስርጭት ሴሚናር ( Dissemination seminar ) የተካሄደ ሲሆን፣ በዚህ ወቅት የዋናው ሪፖርት ኮፒና ሌሎች የተለያዩ ጽሑፎች ለተሣታፊዎች ታድለዋል፡፡ በዕለቱ የሪፖርቱን ይዘት በተመለከተ በመ/ቤቱ ባለሙያዎች የሪፖርቱ ልዩ ልዩ ምዕራፎች ለሴሚናሩ ተካፋዮች የቀረቡ ሲሆን፣ በሴሚናሩም ላይ ከመንግሥት መ/ቤቶች፣ ከMACRO INTERNATIONAL፣ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከምግባረሰናይ ድርጅቶችና ከምርምር ተቋማት የተውጣጡ 180 የሚሆኑ ባለሙያዎች ተሣታፊ ሆነዋል፡፡

## 2.2 የ1996 ዓ.ም አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅትን በተመለከተ

በ1996 ለሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ተግባራት በመካሄድ ላይ ሲሆኑ፣ እነዚህም በቅድመ ቆጠራ የካርታ ሥራ ዝግጅት ላይ ያተኮሩ ሥራዎች ናቸው፡፡ ለሥራው ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል፣ ሎጂስቲክስና በጀት የሚጠይቅ ሲሆን በርካታ ሥራው ወቅት በአገሪቱ የሚገኙትን ቤቶች በሙሉ ያካተተ የካርታ ንድፍ ሥራ ይካሄዳል፡፡ ለዚሁ ሥራ ከውጭ አገር መገዛት ያለባቸው ቁሳቁሶች በ UNFPA በኩል እንዲገዙ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ በተጨማሪ ለካርታ ሥራው የመስክ ሥራና ለዋናው ቆጠራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዝርዝርና አጠቃላይ የፕሮጀክት ዶክመንት ከ UNFPA-CST ከተመደበ ባለሙያ ጋር በመተባበር

በመዘጋጀት ላይ ይገኛል። ይህም ፕሮጀክት ዶክመንት የበጀት ፍላጎትና የሥራ መርሃ-ግብር የያዘ ሲሆን ከተጠናቀቀ በኋላ ለሚመለከተው የመንግሥት አካልና ለዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እንዲደርስ ይደረጋል።

- የ UNFPA አራተኛው ዙር የዕርዳታ ፕሮግራም በ December 2001 ስለሚጠናቀቅ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የሚያገለግል የዕርዳታ ፕሮግራም እየተዘጋጀ በመሆኑ ለቀጣዩ ዙር ፕሮግራም ዝግጅት መ/ቤቱ በአባልነት ተወክሎ በመስራት ላይ ሲሆን በዚህም መሠረት ለቀጣዩ የ1996 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈፀሚያ አስፈላጊውን ዕርዳታ ለማግኘት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

## 2.3 የቫይታል ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- የ1990/91 የቫይታል ስታቲስቲክስ ሰርቬይና ምዝገባ ጥናት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1991/92 ዓ.ም የተሰበሰበው የቫይታል ስታቲስቲክስ ሰርቬይና ምዝገባ መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ፣ የዳታ ኢንትሪ ሥራና የመረጃ ቅንብር ሥራ በማከናወን የስታቲስቲክስ ሠንጠረዦች ተዘጋጅተው የትንተና ተግባር ተጠናቋል። ከዚህ ጥናት የተገኘውን የትንተና ውጤት በመገምገምና በቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ወደፊት ከታሰበው የአጠናን ስልት አንፃር የጥናቱ ውጤት ለአሠራር በሚጠቅም መልኩ ሪፖርቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

## 2.4 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓትና የሕዝብ ምዝገባን በተመለከተ

- ቀደም ሲል በሐረሪ ብሔራዊ ክልልና በድሬዳዋ ካውንስል የቫይታል ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በቀጣይነት ለመሰብሰብና ለማጠናቀር በቀረበው የሙያ ድጋፍ ጥያቄ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቀጣይ ግንኙነት ለማድረግ ተሞክሯል። በተደረጉትም ግንኙነቶች የቫይታል ስታቲስቲክስንም ሆነ የሕዝብ ምዝገባን አግባባዊ (conventional) አሠራሩን እንዲረዱ ተደረጓል።

- ስለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስታቲስቲክስ ሥርዓትና የሕዝብ ምዝገባ ቴክኒካዊ አሠራር በኢትዮጵያ እንዴት ማቋቋምና መተግበር እንደሚቻል ጥልቅ ጥናትና ምርምር ማድረግ የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶችን ያካተቱ ቴክኒካዊ ጽሑፎች የተዘጋጁ ሲሆን ሥርዓቱን ለማቋቋም የበርካታ ሙያዎችን ጥምረት የሚጠይቅ በመሆኑ በተለይ

በሕግና በአስተዳደር ዘርፍ ከመረጃ ሥርዓቱ የሚገኙ ግላዊና ጥቅል መረጃዎች ላይ ያተኮረና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመነጋገር መነሻ የሚሆን ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

- ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ የሙከራ ጥናት ቦታዎችን ለመምረጥና ከአስፈጻሚ ተቋማቱ ጋር ለመስራት የሚያስችል የአሠራር ስልቶችን ለመንደፍ የቅድመ ሙከራ ቅኝት ጥናት ተካሂዷል። ለዚህም በአዲስ አበባ የተመረጡ የጤና ተቋማትና የመስተዳደሩን የቫይታል ስታቲስቲክስ አገልግሎት የሥራ ክፍልን እና የሃይማኖት ተቋማትን ያካተተ የቅኝት ጥናት ተደርጎ ሪፖርቱ ለሚመለከተው ክፍል ቀርቧል።

- በተለያዩ ሀገሮች የሥርዓቱን አወቃቀርና አሠራር የሚያሣይ ጽሑፍ የመጀመሪያ ረቂቅ የተዘጋጀ ሲሆን ሥርዓቱን በማዋቀር በሙያና በአተገባበር ተሣታፊ ከሚሆኑ አካላት ጋር ሙያዊ ምክክር ለማድረግ አልፎም የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር እየተሞከረ ይገኛል።

- የሕዝብ የክብር መዝገብና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓትን በሚቀጥለው ዓመት በተመረጡ 22 ቀበሌዎች ላይ የሙከራ ጥናት ለማድረግ የመዝጋቢዎች መመሪያ እና የተዛማጅ መዝገቦች ዝግጅት በመደረግ ላይ ሲሆን፣ የዚሁ ሥራ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ በባለሙያዎች ተገምግሞና ውይይት ተደርጎበት በማሻሻል ለሁለተኛው ረቂቅ ዝግጅት እንዲውል ተደርጓል።

- የሕዝብ የክብር መዝገብ ምዝገባና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓት የመዝጋቢዎች መመሪያ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

2.5 <u>የሰው ኃይል ስታቲስቲክስን በተመለከተ</u>

- በ1991 በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጠናው የሰው ኃይል ጥናት አናሊቲካል ሪፓርት ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ተሰጥቶና ህትመቱ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። እንደዚሁም የዚሁ ጥናት የስታቲስቲካል ሪፖርቱ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች በመሰራጨት ላይ ይገኛል።

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት የልጆች የሥራ ሁኔታ ጥናት (Stand - Alone Child Labour Survey) እንዲያካሄድ የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) እና የሠራተኛና ማህበራዊ

ጉዳይ ሚ/ር ተስማምተው በጠየቁት መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ የሚረዳው የመጀመሪያ ደረጃ የመስክ ሙከራ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ ለዋናው ጥናት የሚሳተፉ የአሠልጣኞችና የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተጠናቆ በናሙና በተመረጡ 723 የገጠርና 535 የከተማ በጠቅላላው በ1258 የቆጠራ ቦታዎች መረጃ የመሰብሰቡ ተግባር ተጠናቋል፡፡ በመሆኑም የመረጃው ኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ እና የቬሪፊኬሽን ሥራ እንዲሁም መረጃውን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃውን በኮፒውተር ለመተንተን አስፈላጊ የሆኑ የሠንጠረዥ ዝግጅት፣ የትንተና ፕሮግራምና ተዛማጅ ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

2.6 <u>ማህበራዊ ስታቲስቲክስ በተመለከተ</u>

ሀ) <u>የጤናና ትምህርት ስታቲስቲክስ</u>

ለዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆኑ ጤና ነክ መረጃዎችን ከሁለተኛ የመረጃ ምንጭ ( Secondary data source) ለመሰብሰብ እንዲቻል 8 ገጽ መጠይቆችን አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ለክልል ጤና ቢሮዎች ከነሐሴ ወር 1992 ዓ.ም ጀምሮ ተሰራጭቷል፡፡ የአብዛኛው መጠይቆች ይዘትና ብዛት ካለፈው ጋር ተመሣሣይ ቢሆንም ዘንድሮ አንድ አዲስ መጠይቅ ( በየክልሉ ያሉ መድሃኒት ቤቶችና አቅራቢዎች ብዛት የሚያሣይ) ተካቷል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ክልሎች መጠይቆቹን ሞልተው የላኩ ሲሆን የ1992 አንዱ መጠይቅ ( የበሽታዎች ምክንያት የሚለው ) ከተወሰኑ ክልሎች እስካሁን አልተላከም፡፡ ሆኖም ተሞልተው በደረሱት መጠይቆች ላይ አስፈላጊው መሻሻል ከተደረገ በኋላ በ1992 ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲካተቱ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡

ለ) <u>የትምህርት ስታቲስቲክስ</u>

የ1992 ዓ.ም የትምህርት መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መጠይቆች ተዘጋጅተው ለሁሉም ክልሎች የተላከ ሲሆን፣ ሁሉም ክልሎች መረጃውን ሞልተው በመላካቸው ትምህርት ሚ/ር ከሚያወጣው መስል መረጃ ጋር የማመሳከር ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የዚሁ ዓመት የትምህርት መረጃ ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቶ በዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት እንዲወጣ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል፡፡

ሐ) የስፖርት ስታቲስቲክስ

ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ የስፖርት መረጃ በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ያልወጣ በመሆኑ ከ1990 – 1992 ድረስ ያሉትን የስፖርት መረጃዎች በክልል የስፖርት ኮሚሽን ጽ/ቤቶች ለመሰብሰብ መጠይቆች ተዘጋጅተውና ወደ የክልሉ ተልከዋል። በዚሁ መሠረት ሁለት ክልሎች መጠይቆቹን ሞልተው የላኩ ሲሆኝ ከፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ከተገኘ የስፖርት መረጃ ጋር በማካመድ በዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲወጣ ተደርጓል።

መ) የባህል ስታቲስቲክስ

የባህል መረጃን በተመለከተ በባህልና ማስታወቂያ ሚ/ር ለማግኘት ተሞክሮ እስካሁን አልተቻለም። በመሆኑም የባህል መረጃ ክፍተትን ለማጥበብ እንዲቻል መጠይቆች ተዘጋጅተው ለክልል ባህል ቢሮዎች የተላከ ሲሆኝ ሁሉም ክልሎች መረጃውን ሞልተው ልከዋል። ሆኖም የተላኩት መረጃዎች የማይጣጣሙና መመሳከር ያለባቸው ስለሆኑ ከክልል ቢሮዎች ጋር በመገናኘት መረጃዎቹን የማጥራት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

ሠ) የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስ

የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስን መረጃ በየዓመቱ ተዘጋጅቶ በሚወጣው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ለማካተት የ1991 እና የ1992 ዓ.ም የማረሚያ ቤቶችንና የፌደራል ፖሊስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲቻል የተለያዩ መጠይቆች ለሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል መ/ቤቶች ተበትነው ሁሉም መጠይቆቹን ሞልተው የላኩ ሲሆኝ በዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲካተቱ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።

2.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ

- በ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ከጣሊያን ባለሙያዎች ጋር ለሚደረገው የጋራ ጥናት ጥናታዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ረገድ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል። ይህ የትብብር ጥናት በዚህ በጀት ዓመት መጠናቀቅ ስለነበረበት በጥናቱ የተሣተፉ ባለሙያዎች ከጣሊያን አቻዎቻቸው ጋር በሕብረት

ሰባት ጥናታዊ ጽሑፎችን አዘጋጅተው ለአንድ ቀን በተካሄደ ሴሚናር ቁጥራቸው 80 ለሚደርሱ ተሳታፊዎች አቅርበዋል።

- ከሁለተኛ ምንጭ ( Secondary Data) የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል መረጃ ሰጭ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር እየተሞከረ ሲሆን በተጨማሪም በተበተኑ ቅጾች አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በሚገባ ተጠናቅረው ለሚመለከተው ተላልፈዋል።

- ከተለያዩ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ቴክኒካዊ ድጋፍ ተሰጥቷል።

## 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለተጠቃሚዎች አዘጋጅቶ የሚያሰራጫቸው ሪፖርቶች አብዛኞቹ የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ዘርፍ ጥናት ውጤቶች ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምና በግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ሥር ከሚከናወኑት የተለያዩ ጥናቶች ዘርፉን የሚመለከቱ ሪፓርቶችን አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት በዕቅድ ይዟል። በመሆኑም በ1993 ዓ.ም በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎች የዕቅድ አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

#### 3.1.1 ዓመታዊ የግብርና ናሙና ጥናት

##### ሀ. የሰብል ምርት ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- የ1993 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃዎች ተሰብስበውና ለመረጃ ቅንብር የሚያገለግል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎቹ ተዘጋጅተው ከተቀነባበሩና ከተጠናቀሩ በኋላ ለተጠቃሚ በሚሆን መልኩ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1993 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያና የግብርና ናሙና ጥናቶችን አስመልክቶ ከመስክ የሚሰበሰበውን መረጃ ጥራት ለመከታተል ጥናቱ በሚካሄድባቸው ቦታዎች የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በመዘዋወር የቁጥጥር ተግባር አከናውነዋል።

ለ. <u>የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ</u>

- የ1992 የመኸር ሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1992 ዓ.ም በበልግ ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን መረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የቅንብር ሥራ ተጠናቆ የጥናቱ ውጤት ሪፓርት የሕትመት ሥራው ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1993 ዓ.ም የመኸር ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ሕትመቱ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ሪፖርቱም ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። እንዲሁም ለዚሁ ዓመት የበልግ ወቅት መረጃ የሚያገለግል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ሐ. <u>የእርሻ ሥራን /Farm Management Practices/ በተመለከተ</u>

- የ1992 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት እርሻ ሥራ አጠቃላይ ሪፓርት ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1992 ዓ.ም የበልግ እርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ተሰብስቦ የቅንብር ሥራ ላይ ይገኛል።

- የ1993 ዓ.ም የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፓርት ተጠናቆ ለሕትመት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቷል።

መ. <u>የመሬት አጠቃቀምን /Land Utilization/ በተመለከተ</u>

- የ1992 የመሬት አጠቃቀም ሪፓርት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1993 የመሬት አጠቃቀም ሪፖርት መረጃ ከመስክ ተሰብስቦና ተቀነባብሮ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት ተዘጋጅቶ የመረጃው አስተማማኝነት በመገምገም ላይ ይገኛል ።

ሠ. <u>የቤት እንስሳት፡ ዶሮና ንብ የያዙ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

- የ1992 ዓ.ም የቤት እንስሳት መረጃዎች ቅንብርና የሪፓርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- የ1993 ዓ.ም የቤት እንስሳት ጥናት መረጃ ተሰብስቦ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቋል፡፡

3.1.2. <u>የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናትን በተመለከተ</u>

ሀ. በ1992 ዓ.ም በተካሄደው የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ላይ በመረጃ መሰብሰቡና ቅንብሩ ወቅት በተገኘው ተሞክሮና ከውጭ መጥተው በነበሩ ኤክስፐርቶች በተሰጠው የማሻሻያ ሃሣቦች መሠረት የቆጠራው ዶክመንቶች በ1993 ዓ.ም ለተካሄደው የሙከራ ቆጠራ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ለ. በ1992 ዓ.ም ተካሂዶ በነበረው የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ተሰብስበው የነበሩ የከተማ ሙከራ ጥናት መረጃ፣ የበልግ ወቅት የመንግሥት፣ የግል የንግድ እረሻዎች መጠይቆች መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ተግባር ተጠናቋል፡፡ ከከተማ የግብርና ሙከራ ቆጠራ የተገኘውም መረጃ ቅንብር ተጠናቆና ውጤቱ ተገምግሞ በቀጣዩ የግብርና ቆጠራ የከተማ መጠይቅ ላይ ተገቢ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

ሐ. በ1993 ዓ.ም በሦስት ወረዳዎች በተካሄደው የግብርና ናሙና ሙከራ ቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ የቬሪፊኬሽን ሥራና መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ተግባር የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የክሊኒንግ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ በመሆኑም የተወሰኑ መረጃዎች የቅንብር ሥራ ተጠናቆ ውጤቱ በመገምገም ላይ ይገኛል፡፡

መ. በ1993 ዓ.ም የግብርና ናሙና ሙከራ ቆጠራ ከመስከ ለተሰበሰቡና ወደፊትም በዋናው ቆጠራ ለሚሰበሰቡ መረጃዎች የኮምፒውተር ቅንብር ቀደም ብሎ የተዘጋጀውን የኮምፒውተር ኤዲት ስፔስፊኬሽን የማሻሻልና የማጠናቀቅ ሥራ ለገጠርና ለከተማ መጠይቆች ተከናውኗል፡፡ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን በተመለከተ በቀጣይነት ለመሥራት አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ሠ. የ1993 ዓ.ም የግብርና ናሙና ሙከራ ቆጠራ ጥናት በሚካሄድባቸው ወረዳዎች በባለሙያዎች የመስክ ቁጥጥርና ክትትል የተደረገ ሲሆን፣ በUSAID ትብብር የተላኩ አንድ አማካሪም የሙከራው ጥናት ከሚካሄድባቸው በአንዱ ወረዳ የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉ በማድረግ የዝግጅት ሥራውን እንቅስቃሴ ግንዛቤና ሙያዊ እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል።

ረ. ለ1994 ዓ.ም. ለሚካሄደው ቆጠራ የተለያዩ የሰብል አጨዳ ማሳ መጠንን በተመለከተ በ1993 ዓ.ም. ከተካሄደው የግብርና ሙከራ ተሞክሮ በመነሣት አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች ተዘጋጅተው በመመሪያው ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።

ሰ. ለ1994 ዓ.ም. የግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያገለግል የስፋትና የምርት አካባቢ መለኪያ ኮድ ቡኮች ዝግጅት ተጠናቆ ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል።

ሸ. ለ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ የሚውሉ መጠይቆችና መመሪያዎች የመጨረሻ መልካቸውን እንዲይዙ ከማድረጉም በላይ የመጠይቆች ሕትመት በአብዛኛው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ለሥልጠና የሚሆኑ መመሪያዎችና መጠይቆችን የማሰራጨቱ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል።

ቀ. ለ1994 ግብርና ናሙና ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን የሚያከናውኑ ሰባት የቴክኒክ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ የተደረገ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ኮሚቴ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የመጠይቅ፣ የመመሪያና የሌሎች አሠራር መመሪያዎችን ዝግጅት ሥራ አከናውነዋል። ከእነዚህ ኮሚቴዎች በተጨማሪም ሌሎች ሦስት ኮሚቴዎች ማለትም የሎጂስቲክስ፣ የሰው ኃይል ማደራጃና የትራንስፖርት ኮሚቴዎች ተቋቁመው በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የዝግጅት ሥራዎችን በመስራት ላይ ሲሆኑ፣ እንደ ሌሎቹ ኮሚቴዎች ወቅታዊ ሪፖርታቸውን ለዋናው የግብርና ቆጠራ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ።

### 3.1.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

ሀ. ለዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚውሉ የግብርናና ሌሎች ግብርና ነክ የሆኑ መረጃዎች ከሌሎች ድርጅቶች አሰባስቦና አቀነባብሮ ለሕትመት በሚሆን መልክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ቀርቧል::

ለ. ለ1993 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያና የግብርና ናሙና ጥናት የሚያገለግሉ መጠይቆችና መመሪያዎች በማዘጋጀት ለየቅ/ጽ/ቤቶች ተሰራጭተው እንዲሰራባቸው የተደረገ ሲሆን፣ ለዚሁ ዓመት የግብርና ቆጠራ ጥቅም ላይ በሚውል የሜቶዶሎጂ ዝግጅት ላይ ተከታታይ ውይይት ተካሂዷል::

ሐ. ከተለያዩ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚቀርቡ ግብርና ነክ የመረጃ ጥያቄዎችን በማስተናገድ ላይ ይገኛል::

## 3.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ዓለም አቀፍ የአሠራር ዘዴዎችን በመከተል የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር ውጤታቸው ወቅቱን ጠብቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ የሚደረግ ሲሆን፣ በ1993 በጀት ዓመት በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎችም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

### 3.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶችን ሥራ በተመለከተ

#### ሀ. በከተሞች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

ከመስከረም 1992 እስከ ታህሣስ 1992 ዓ.ም ድረስ ያለው ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለሕትመት የተላከ ሲሆን፣ ከጥር እስከ ሰኔ 1992 ዓ.ም ድረስ ያለው ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለሕትመት ተዘጋጅቷል:: እንደዚሁም ከሐምሌ 1992 እስከ መጋቢት 1993 ዓ.ም ያለው ሪፖርት ተጠናቆ ለሕትመት የተዘጋጀ ሲሆን፣ የሚያዚያ ወር 1993 ዓ.ም መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጀምሯል::

ለ. <u>በገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

ከጥቅምት 1992 እስከ ሰኔ 1992 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ሪፖርት ለሕትመት የተላከ ሲሆን፣ ከሐምሌ 1992 እስከ መጋቢት 1993 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ የማቀነባበር ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ተዘጋጅቷል። እንዲሁም የሚያዚያ ወር 1993 መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ በመሠራት ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት</u>

ከመስከረም 1992 እስከ የካቲት ወር 1992 ድረስ ያለው መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ የታተመ ሲሆን፣ ከመጋቢት እስከ ሰኔ 1992 ዓ.ም ድረስ ያሉት መረጃዎች ሪፖርት ተጠናቀው ለሕትመት ተዘጋጅተዋል። እንዲሁም ከሐምሌ 1992 እስከ መጋቢት 1993 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ ለሕትመት ዝግጁ ሲሆን፣ የሚያዚያ ወር 1993 መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል።

መ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ</u>

- የአገር አቀፍ፣ የገጠርና የከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክሶች

  - የ1993 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ ድረስ ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፣ የግንቦት ወር 1993 ዓ.ም. ኢንዴክስ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል።

- የአዲስ አበባ ከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ

  - የ1993 ዓ.ም እስከ ግንቦት ድረስ ያለው ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተጠናቀውና ታትመው ለተጠቃሚ የተሰራጩ ሲሆን፣ ሰኔ ወር 1993 ዓ.ም ኢንዴክስ ደግሞ ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል።

### 3.2.2 የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት

በ1991 ዓ.ም ሰኔና ሐምሌ ወራት ላይ የተካሄደው አንደኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት እንዲሁም በጥርና በየካቲት 1992 የተካሄደው ሁለተኛ ዙር የዚሁ ጥናት የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራ ተጠናቆ የመጀመሪያ ድራፍት ሪፖርት ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚ/ር የቀረበ ሲሆን፣ የዚሁ ጥናት ውንጠረዦች ለሕትመት በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተዋል።

### 3.2.3 የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደህንነት ጥናት

በ1992 ዓ.ም ጥርና የካቲት ወራት ላይ ከሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ጋር የተካሄደው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የመረጃ ማቀነባበር ሥራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ለሕትመት በሚሆን መልክ ተዘጋጅቷል።

### 3.2.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

#### ሀ. የሸማቾች ዋጋ ኢንዴክስ ( Consumer Price Index ) ዝግጅት

በ1991/92 የተካሄደውን የቤተሰብ በጀት ጥናት ውጤት መሠረት በማድረግ ከሐምሌ ወር 1993 ዓ.ም ጀምሮ በአገር አቀፍ፣ በክልሎች፣ በድሬዳዋ አስተዳደር ም/ቤትና በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ የሸማቾች ዋጋ ኢንዴክስ ለማዘጋጀት እንዲቻል የሚከተሉት ተግባራት በበጀት ዓመቱ ተከናውኗል። እነዚህም፡-

- የሸማቾች ዋጋ ኢንዴክስ ስሌት የሚያገለግሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ( Basket of Commodities ) መረጣ፣ እና
- የተመረጡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከጠቅላላው የቤተሰቦች ወጪ ያላቸው የመቶኛ ድርሻ ስሌት ( Weight Construction ) ዝግጅት ናቸው።

#### ለ. የችርቻሮ ዋጋ ጥናት የአጠናን ስልት መቀየር

የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠር ለተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተመረጡ 1450 የቆጠራ ቦታዎች መካከል በ446 በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎችና

በ26 ከተሞች በየወሩ ይካሄድ እንደነበር ይታወቃል ። ይሁን እንጂ የገጠሩ የዋጋ ጥናት መረጃዎች በተለያዩ በርካታ ምክንያቶች ማለትም:-

1. በገጠር የተመረጡት የገበያ ቦታዎች ለዋጋ ጥናት ተብለው የተመረጡ ሳይሆን ለግብርና ናሙና ጥናት የተመረጡ ቤተሰቦች የሚገኙባቸው ገበያዎች በመሆናቸውና እነዚህም በአሁኑ ጊዜ ባለው የነፃ ገበያ መሠረት የዋጋ ውጣ ውረድ በትክክል ሊያሳዩ ባለመቻላቸው፤

2. ለግብርና ናሙና ጥናት የሚመረጡት ቦታዎች በአብዛኛው የአገሪቱን የገጠሩን ክፍል ብቻ ስለሚወክሉ የገበያ ቦታዎቹ የሚይዙት ዕቃዎችና አገልግሎቶች መጠን አናሳ በመሆናቸው፤ እንዲሁም ገበያዎቹ የሚገኙባቸው ቦታዎች በጣም ሩቅ ስለሆኑ ( Remote Areas ) መረጃዎቹን አሰባስቦና አጠናቅሮ ሪፖርቱን ለተጠቃሚው ለማሰራጨት አዳጋች በመሆኑ፤

እነዚህን ችግሮች ለዘለቄታ ለመፍታት ሲባል መ/ቤቱ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችችን ሲያከናውን ቆይቷል። በመሆኑም የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል። እነዚህም:-

- በየዞኑ የደራ የገበያ ቦታ ያላቸው 170 ከተሞችን በመምረጥ የሙከራ የዋጋ ጥናት ማካሄድ፤
- አማካይ የዋጋዎች መረጃን መሠረት በማድረግ ከ170 ከተሞች መካከል 119 የገበያ ቦታዎችን በ106 ከተሞች በመምረጥ ለሚቀጥሉት 5 ዓመታት የሚወጡ Consumer Price Index በአገር አቀፍ ደረጃ፤ በክልል ደረጃና በአዲስ አበባ ከተማ እንዲዘጋጁ ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- ለዋጋ ጥናት የሚያገለግሉ ዶክመንቶች /የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ፤ የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያና የዋጋ ጥናት መጠይቅ/ ማዘጋጀትና ማሳተም፤
- በየከተማው ለሚመደቡ መረጃ ሰብሳቢዎችና ለሌሎች ጥናቱ የሚመለከታቸው ሠራተኞች በአዲስ አበባ ከተማ ስልጠና መስጠት፤ እና

- ከላይ የተገለፁ ተግባራትን በማጠናቀቅ ከሐምሌ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ መረጃ የመሰብሰቡ ሥራ እንዲጀመር ዝግጅት ማጠናቀቅ የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህንን የአሠራር ስልት በተመለከተ አንድ ከIMF የመጡ ባለሙያ ለመ/ቤቱ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጥተዋል።

ሐ. <u>የግብርና ውጤት የአምራች ዋጋ ጥናት</u>

- የሥራ መደራረብን ለመቀነስ የአምራች ዋጋ ጥናት የሚመለከታቸው የቆጠራ ቦታዎችንና የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት የሚካሄድባቸውን የቆጠራ ቦታዎች የተለያዩ በማድረግ የናሙና ምርጫው የተካሄደ ሲሆን፣ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ታትሟል።

- ለአምራች ዋጋ ጥናት የሚያገለግል መጠይቅ ተዘጋጅቶ ታትሟል።

- መረጃውን የሚሰበስቡት ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሚቀጠሩ መረጃ ሰብሳቢዎች ስለሚሆኑ በየሥልጠና ማዕከላቱ የአምራች ዋጋ ጥናት መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና እንዲሰጣቸው የሥልጠና ቁሣቁሶች ተዘጋጅተው እንዲታተሙ የተደረገ ሲሆን፣ የአምራች ዋጋ ጥናት የመረጃ መሰበሰብ ተግባርም የሚጀመረው ከመስከረም 1994 ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ ይሆናል።

## 3.3 <u>የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

### 3.3.1. <u>የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

- የ1991 ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት በተመለከተ በመጋቢት ወር 1992 በተካሄደው ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የዳታ ኢንትሪና የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1992 ዓ.ም የዘርፉ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ፣ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ የውንጠረዥ ቅንብር ሥራ በመሠራት ላይ ይገኛል።

ለ. <u>የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

የ1991 ዓ.ም የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪን በተመለከተ በመጋቢት ወር 1992 ዓ.ም በተካሄደው ጥናት የተሰበሰበው መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ በዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መጽሔት ውስጥ ተካትቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። የዘርፉ የ1992 ጥናት መረጃ ተሰብስቦ በመጠናቀር ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>የኮንስትራክሽን አጠቃላይ ቆጠራን በተመለከተ</u>

የ1991 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ጥናትን በተመለከተ መረጃው በሚያዚያ ወር 1992 ዓ.ም በተካሄደው ጥናት ከመስክ ተሰብስቦ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ እንዲሁም የመረጃ ቅንብር ሥራው ተጠናቆና ታትሞ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

መ. <u>የማዕድን ቁፋሮ ጥናት</u>

የ1991 ዓ.ም ዘርፉን በተመለከተ መረጃው በግንቦት ወር 1992 ዓ.ም በተካሄደው ጥናት የተሰበሰበ ሲሆን፣ የመረጃ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ መረጃውን የማጥራት ሥራ ተጠናቋል።

ሠ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ኢንዴክስ ሥራ የመረጃ ቅንብርና የትንተና ሥራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል። የ1992 ዓ.ም መረጃን የሚያካትተው የኢንዴክስ ሥራ የመረጃ ቅንብር ሥራ ተጠናቋል።

- ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃና

የማዕድን ምርት መረጃዎች ቅንብር ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ቀርቦ መጽሔቱ ታትሟል።

- በተጨማሪም ሁሉም ዘርፎች እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ለመረጃ ተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠትና አጠቃቀሙን የማስረዳት ሥራ ተከናውኗል።

3.3.2 <u>የንግድ፣ የትራንስፓርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃ</u>

- የ1990/91 ዓ.ም የትራንስፓርትና መገናኛ መጽሔት መረጃ ቅንብርና የትንተና ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1991/92 የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት መረጃ ቅንብርና የትንተና ሥራ ተከናውኖ ለሕትመት ተልኳል።

- የውጭ ንግድ የመጀመሪያው መጽሔት እ.ኤ.አ የ1997 - 1999 ያለውን መረጃ የያዘ ሪፓርት ተቀነባብሮና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን፣ የውጭ ንግድ ኢንዴክስ መጽሔት ደግሞ የመረጃ ቅንብርና ትንተና ሥራው ተጠናቆ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል። እንዲሁም እ.ኤ.አ የ2000 መረጃ የያዘው መጽሔት በዝግጅት ላይ ይገኛል።

- በዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚወጣ የውጭ ንግድ ስታቲስቲክስ፣ የፋይናንስ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ መረጃ ተሰብስቦና ተጠናቅሮ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል።

## በ1993 በጀት ዓመት የጥናቶች የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

ሠንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1992 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የ1993 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | የግብርና ናሙና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የ1993 የግብርና ሰብል ትንበያ | አዲስ | 11 | 89 | 89 | 100 |
| 1.2 | የ1993 የግብርና ናሙና ጥናት | አዲስ | 11 | 89 | 89 | 100 |
| 1.3 | የ1992 የግብርና ናሙና ጥናት | ነባር | 90 | 10 | 10 | 100 |
| 2 | የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት | | | | | |
| 2.1 | የሰብል ናሙና ጥናት | አዲስ | 10 | 90 | 90 | 100 |
| 2.2 | የግል የገበሬ ይዞታን በተመለከተ | " | 10 | 90 | 90 | 100 |
| 2.3 | የቤት እንስሳት እርቢ አካባቢን በተመለከተ | " | - | 100 | 100 | 100 |
| 2.4 | የመንግሥት፣ የግል ንግድና ኅብረት እርሻ | " | - | 65 | 65 | 100 |
| 3 | የዋጋዎች ጥናት | | | | | |
| 3.1 | የ1992 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ | ነባር | 93 | 7 | 7 | 100 |
| 3.2 | የ1992 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ በገጠር | ነባር | 93 | 7 | 7 | 100 |
| 3.3 | የ1993 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 15 | 80 | 80 | 100 |
| 4 | የ1992 የዲሞግራፊና ጤና ጥናት | ነባር | 78 | 22 | 22 | 100 |
| 5 | የ1992 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት | ነባር | 72 | 28 | 28 | 100 |
| 6 | የ1992 የኮንስትራክሽን ጥናት | ነባር | 65 | 35 | 35 | 100 |
| 7 | የ1992 የማዕድን ቁፋሮ ጥናት | ነባር | 65 | 35 | 35 | 100 |
| 8 | የ1993 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ጥናት | አዲስ | - | 87.6 | 87.6 | 100 |
| 9 | ዋጋዎች ኢንዴክስ ሥራ | | | | | |
| 9.1 | በአገር አቀፍ ደረጃ የዋጋ ኢንዴክስ በከተማ | አዲስ | - | 90 | 76.7 | 85.2 |
| 9.2 | የአዲስ አበባ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 100 | 92.4 | 92.4 |

## 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ

### 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ሥራን በተመለከተ

መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችንና የአፈፃፀም መመሪያዎችን እንደዚሁም ለጥናቶቹ የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ ብቃትና ወካይነታቸውን በማረጋገጥ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የሚደረግ ሲሆን በ1993 በጀት ዓመትም ተመሣሣይ ተግባራት ተከናውነዋል::

#### ሀ. የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- በ1992 ዓ.ም ለሚካሄዱት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናትና የበልግ የግብርና ናሙና ጥናት የማባዣ (weight) ሥራ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሰጥቷል::

- የ1993 ዓ.ም የግብርና ናሙና ጥናት የትንበያ፣ የመኸርና ለእንስሳት ጥናት የሚያገለግሉ የሚባዣ ሥራዎች ተሠርተው ተጠናቀዋል:: እንዲሁም ለ1993 የግብርና ናሙና ጥናት በጥናቱ የሚሸፈኑ የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር የያዘ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሰራጭቷል:: በተጨማሪም የ1993 ዓመታዊ ግብርና ናሙና ጥናቶች ሣምፕል ዲዛይን ሪፖርቶች ተዘጋጅተው ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል::

- የማባዣ (weight) ሥራ ለተዘጋጀላቸው የናሙና ጥናቶች ውጤቶች ለተጠቃሚዎች ከመሰራጨታቸው በፊት አስፈላጊው ግምገማ በባለሙያዎች ተደርጓል::

#### ለ. የግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናትና የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ የዝግጅት ሥራዎች

- ለግብርና ናሙና ጥናት በተመረጠው ዲዛይን ላይ ተጨማሪ ፍተሻ (Refinement) ለማካሄድ አንዳንድ ውሣኔ በሚፈልጉ የሳምፕሊንግ ፕላን ነጥቦች

ላይ የክፍሉ ሠራተኞች ከUSAID ከመጣው አማካሪ ጋር በመሆን ለመነሻ የሚረዱ የሳምፕሊንግ ዲዛይን በሦስቱ የተመረጡ ወረዳዎች ተሰርቷል።

- ቀደም ሲል ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ለቤተሰቦች መመዝገቢያ በተዘጋጀው መመሪያ ላይ በመመርኮዝ ጽንሰ ሀሣቡን ሳይለቅ ሌላ አዲስ አሠራርና ቀለል ያለ የቤተሰቦች መመዝገቢያና የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቶ፣ ይህንኑ መመሪያ መሰረት በማድረግ የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ጥናቶቹ በሚካሄድባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በመገኘት ለመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎችና ለመረጃ ሰብሳቢዎች አስፈላጊው ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ የመስክም ግምገማ ተካሂዷል።

- ለ1994 ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ ዝግጅት ከተቋቋሙት የቴክኒክ ኮሚቴዎች የተላለፉ የዲዛይን ሥራዎች አብዛኞቹ የተጠናቀቁ ሲሆን ለከብት አርቢ አካባቢዎች ለሚካሄደው ቆጠራ የጥናት ዲዛይን በመገምገም ላይ ይገኛል።

- ለ1994 ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የሚሆን ሜቶዶሎጂ አጠቃላይ Recommendation የተዘጋጀ ሲሆን፣ ለዋናው ቆጠራ ዝግጅት በመካሄድ ላይ ላለው የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት የትንበያና የመኸር ጥናት የማባዣ ሥራ ተጠናቋል።

- ለ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ እንዲያገለግል በታቀደው መሠረት እስከ 1992 ድረስ የተደረጉ የድንበር ሽግሽግና ለውጥ መሠረት ማስተር ፍሬም የማስተካከል ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ እስከ ግንቦት 30/1993 ድረስ የተደረጉ የዞን፣ የወረዳና የገ/ማኅበራት ሽግሽግ በቅ/ጽ/ቤቶች አማካይነት ተሰብስቦ ማስተር ፍሬሙ ተስተካክሎ ለናሙና ምርጫ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል።

- በ1994 ለሚደረገው የግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያገለግል የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ምርጫ የተከናወነ ሲሆን፣ ለናሙና ቆጠራ ቦታዎች ካርታ ዕድሳትና ቤተሰብ ምዝገባ ሥራ ተካሂዷል። እንደዚሁም በሁሉም እርከኖች ላይ ለሚዋቀሩ የቆጠራ አስፈፃሚዎች የሚጠቀሙበት የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ታትሟል።

- በመካሄድ ላይ ላለው የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ካርታ ወቅታዊ ማድረግና ለቤተሰብ ምዝገባ ሥራ የሚረዳ ማንዋል ተዘጋጅቶ ለአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ካርታ ወቅታዊ ማድረግ ሥራ በተሰራበት ወቅት የተከናወነው የቤተሰብ ምዝገባ ውጤት ማጠቃለያ ከተሰራ በኋላ ለ1994 ሰብል ትንበያ ለተመረጡ ቆጠራ ቦታዎች መረጃው ኮምፒውተር ኢንትሪ እየተደረገ ይገኛል።

- ለ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ ሥልጠና የቤተሰቦች መመዝገቢያ፣ የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥ መመሪያና ቅጽ በማዘጋጀት ለአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሐ. <u>ሌሎች ጥናቶችን በተመለከተ</u>

- መ/ቤቱ በ1992 ላካሄደው የ1991 የማዕድንና ቁፋሮ ናሙና ጥናት የሚሆን የማባዣ ሥራ በዲዛይኑ መሠረት የተዘጋጀ ሲሆን፣ የጥናቱ ሣምፕል ዲዛይን ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።

- በ1993 ዓ.ም. በመካሄድ ላይ ላለው የሕፃናት ሥራ ሁኔታ ጥናት የሚሆን የሰርቬይ ሜቶዶሎጂ ተዘጋጅቶ በዲዛይኑ መሠረት የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ምርጫ ተከናውኗል። የጥናቱን ናሙና ቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር የያዘ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የተሰራጨ ሲሆን፣ ለጥናቱ ማባዛት ሥራ ለማዘጋጀት አስፈላጊው ግብአቶች በኮምፒዩተር ኢንትሪ ተደርገው ማባዣውን ለመሥራት የዳታ ክሊኒንግ ውጤት እየተጠበቀ ነው።

- መ/ቤቱ እየተጠቀመበት ያለውን የዋጋ ጥናት ሰርቬይ ሜቶዶሎጂ በመገምገም ወደፊት ሊሰራበት የሚችል ሌላ አዲስ ዲዛይን ተዘጋጅቶና ናሙና ገበያዎች በዲዛይኑ መሠረት በ170 ወካይ የዞን ከተሞች ላይ ተመርጠው በተሰበሰበው የመጀመሪያ ጥናት መረጃ መሠረት ዲዛይኑ ከተፈተሸ በኋላ የናሙና ገበያዎች ምርጫ ተጠናቋል።

## 4.2 የካርቶግራፊ ሥራን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተለያዩ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲቻል ለናሙና መረጣ እንደፍሬም (Sampling Frame) የሚያገለግሉ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች፣ የስታቲስቲክስ መረጃ ውጤቶች የሚያመለክቱ ልዩ ልዩ ግራፎች፣ ቻርቶች እና ሥዕላዊ መግለጫዎች እንደዚሁም ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ ቲማቲክ ካርታዎች፣ ለስታቲስቲክስ ጥናት የሚያስፈልጉ የአስተዳደር ክፍሎችን፣ የቦታ ስሞችን፣ አዳዲስ ከተሞችንና የገጠር አሰፋፈር ሁኔታ (Settlement Pattern) ለውጥ ለመከታተል የካርታዎችን ወቅታዊነት በመጠበቅ አስተካክሎ ያዘጋጃል፡፡ በመሆኑም በ1993 የበጀት ዓመት የሚከተሉትን ሥራዎች አከናውኗል፡፡ ይኸውም፡-

- በ1፡2,000,000 መስፈርት የኢትዮጵያ ካርታ በክልልና በዞን እንዲሁም ዋና ዋና የመኪና መንገዶችንና የከተሞችን አቀማመጥ የሚያሣይ ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡

- በ1፡250,000 መስፈርት ካርታ ላይ የሎንግቲውድና ላቲቲውድ መስመሮች በሁለት ክልሎች ማለትም በትግራይና በአማራ ካርታ ላይ ተሠምረዋል፡፡

- በ1፡250,000 በ3 ክልሎች ማለትም በትግራይ፣ አማራና በቤንሻንጉል ጉምዝ ካርታ ላይ የከፍታ /Elevation/ ከንቱሮች ሥራ ተጠናቋል፡፡

- የጂኦግራፊና የመንደር ስሞች ዝርዝር (ጋዝተር) ለማዘጋጀት በ32 ዞኖች ተሰርቷል፡፡

- የደቡብ ሕዝቦች፣ የአማራ፣ የኦሮሚያና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል የመተከል ወረዳ በአዲሱ የገበሬ ማኅበራት ቅንጅት መሠረት አዲስ ኮድ ተሰርቷል፡፡

- ሙያዊ እገዛና ምክር ለጠየቁ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከአገልግሎቱ አስፈላጊው ምክር ተሰጥቷቸዋል፡፡

- የበልግ አምራች ወረዳዎች ገ/ማህበራትና የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር ዝግጅት የ11 ዞኖች ተጠናቋል፡፡

- በ1994 ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ የተመረጡትን የ11,329 የቆጠራ ቦታ ካርታዎችን ለይቶ በማውጣት ለካርታ ማሻሻል ሥራ ወደ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲላክ ተደርጓል።

- በአገሪቱ የሚገኙትን ወረዳዎች የአስተዳደር አደረጃጀት ለማወቅና ወቅታዊ ለማድረግ እንዲቻል ለቅ/ጽ/ቤቶች የተላከው መጠይቅ ምላሽ ያገኘ ሲሆን፣ በዚሁም መሠረት የአስተዳደር አደረጃጀቱን ወቅታዊ በማድረግ ለሚመለከተው ክፍል እንዲቀርብ ተደርጓል።

## 4.3. <u>የመዛግብት አያያዝና ስታንዳርድስ ተግባራትን በተመለከተ</u>

- በመ/ቤቱ ለተካሄዱ ጥናቶች አገልግሎት እንዲውል ለመረጃ ሰብሳቢዎች ተዘጋጅተው የነበሩ መመሪያዎች አንድ ወጥ የሆነ የኮድ ሥርዓት የሚዘጋጅበት መንገድ እየተጠና ይገኛል።

- በመ/ቤቱ በሚካሄዱ ጥናቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ ፅንሰ ሐሳቦችና ፍቺዎችን በተመለከተ ከአለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር ለማጣጣም በየመስኩ ካሉ አለም አቀፍ ድርጅቶች አግባብ ያለው የማገናዘቢያ ዶክመንት ለማግኘት ተሞክሮ ለጥቂት መምሪያዎች የተገኘ ሲሆን፣ ከእነዚህ ዶክመንቶችም ለተለያዩ ጥናቶች የሚረዱ ማገናዘቢያ ፅንሰ ሃሣቦች ላይ ጥናት እየተደረገ ይገኛል። በተጨማሪም ተመሣሣይ የማገናዘቢያ ዶክመንት ለሌሎቹ መምሪያዎች የጥናት ሥራ ለማግኘት እየተሞከረ ሲሆን፣ ከተገኙትም ማገናዘቢያ ዶክመንቶች ለተለያዩ ጥናቶች የሚሆኑ ማገናዘቢያ ፀንሰ ሃሣብ፣ ላይ ጥናት እየተደረገ ነው።

- መ/ቤቱ በሚያወጣቸው የተለያዩ ሪፖርቶች ላይ አንድ ወጥ የሆነ የብሔር ብሔረሰቦች፣ የክልሎች፣ የዞኖችና የወረዳዎች በአማርኛና በእንግሊዝኛ ትክክለኛ ስምና ቅደም ተከተል ከፌዴሬሽን ም/ቤት ተጠይቆ የተገኘ ሲሆን፣ ይህም መረጃ ለመ/ቤቱ የሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስ ተደርጓል።

- ከጥራትና ደረጃዎች መዳቢ ባለሥልጣን ጋር በመነጋገር quality mamagement standards በሚል ርዕስ ለሥራው አግባብ ላላቸው የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሥልጠና የሚሰጥበት መንገድ እየተሞከረ ይገኛል።

- የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ በሚያወጣው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መፅሔት (Statistical Abstract) የመረጃዎች ቅደም ተከተል በInternational Standard Industrial Classification (ISIC) መሠረት የሚስተካከልበት መንገድ እየተጠና ነው::

- የንግድ፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃን በመ/ቤቱ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ ለማውጣት መረጃዎቹን ገምግሞ ልዩነታቸውን በምን መልኩ ማጣጣም እንደሚቻል ጥናት እየተደረገ ይገኛል::

- በ1994 ዓ.ም. በሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ መከተት ያለባቸው አርዕስቶች በቅደም ተከተል እንዲካተቱና በአርዕስቶች ስም የሚብራሩት ደግሞ ከአለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር የሚጣጣሙ ፅንሰ ሃሣቦች በሚመለከተው መመሪያ በኩል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ለመ/ቤቱ ማኔጅመንት ቀርቧል::

## 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ-ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች ለሚይዘው ለዚህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመሰብሰቡ ተግባር ተጠናቋል:: በመሆኑም ዓመታዊ መጽሔቱ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ለተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቶና ለሕትመት ዝግጁ ሆኖ ታትሞ ለተጠቃሚዎች በመሰራጨት ላይ ይገኛል::

መጽሔቱ በሚዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያካትት የተደረገ ሲሆን እነዚህም:-

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሀገር ሀብት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣

- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የውጭ አገር ንግድ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

### 6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ

በ1993 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,465 ቋሚና 1,811 የኮንትራት በጠቅላላው 3,276 ሠራተኞች ነበሩ ። ከነዚህ የሰው ኃይል ውስጥ ባለፉት አሥራ ሁለት ወራት 51 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የለቀቁ፣ 27 ሠራተኞች በሞት የተለዩ እንደዚሁም 7 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ ሲሆን የ100 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል። በሌላ በኩል 774 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 33 ጀማሪ ስታቲስቲሺያኖች፣ 16 ዳታ ኢንትሪ ኦፕሬተሮች፣ 25 የፐርሰኔል ሠራተኞች እንደዚሁም 15 ሹፌሮች በድምሩ 863 አዲስ የኮንትራት ሠራተኞች ሲቀጠሩ 1009 ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ተሰናብተዋል። በመሆኑም በመ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 3,145 ሲሆን ከእነዚህ መሐል 1,480 ቋሚና 1,665 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። በመ/ቤቱ በበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ላይ ቀርቧል።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ

ሠንጠረዥ 2

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,465 | 1,811 | 3,276 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 100 | 863 | 963 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (7) | - | (7) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (51)* | (1009) | (1060) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (27) | - | (27) |
| | ድምር | **1,480** | **1,665** | **3,145** |

* በበጀት ዓመቱ 13 ባለሙያዎች መ/ቤቱን ለቀው ሄደዋል።

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 135 ፕሮፌሽናል፣ 938 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 407 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው:: የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,120 ወንዶች /75.7 በመቶ/ ሲሆን 360 ሴቶች /24.3 በመቶ/ ናቸው:: በተመሣሣይ ሁኔታ የኮንትራት ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 66 ፕሮፌሽናል፣ 1,427 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 172 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,211 ወንዶች /72.7 በመቶ/ 454 ሴቶች /27.3 በመቶ/ ናቸው::

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ</u>

<u>ሠንጠረዥ 3</u>

| | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፆታ | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ጠቅላላ ድምር |
| ወንድ | 115 | 827 | 178 | 1,120 | 61 | 981 | 169 | 1,211 | 2,331 |
| ሴት | 20 | 111 | 229 | 360 | 5 | 446 | 3 | 454 | 814 |
| ድምር | 135 | 938 | 407 | 1,480 | 66 | 1,427 | 172 | 1,665 | 3,145 |

## 6.2 <u>የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ</u>

በየጊዜው እያደገ የሚመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል በስታቲስቲክስ መረጃ ዝግጅትና በሌሎች ተመሣሣይ ሥራዎች ብቁ ባለሙያ ለማግኘትና ያላቸውንም ዕውቀት ከፍ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት በ1993 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል::

ሀ. በ1993 ዓ.ም ለሚካሄደው በገጠር የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የአሰልጣኞች ሥልጠና ከሐምሌ 27 እስከ ነሐሴ 10 ቀን 1992 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት የተካሄደ ሲሆን በሥልጠናውም ላይ ከተለያዩ መምሪያዎች 48 ባለሙያዎች፣ እንዲሁም ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ 84 በጠቅላላው 132 ሠልጣኞች ተካፋይ ሆነዋል:: በተመሣሣይ ሁኔታ ለመስክ ሠራተኞች በ22ቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከነሐሴ 15 እስከ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል::

ለ. ባለፈው ዓመት የተካሄደውን የግብርና ቆጠራ ሙከራ ጥናት ውጤት ይበልጥ የተሟላ ለማድረግ በዚህ ዓመትም ከአማራ፣ ከኦሮሚያና ከደቡብ ሕዝቦች በናሙና በተመረጡ ሦስት ወረዳዎች ( ቀወት፣ ሳሲጋና የም ልዩ ወረዳ) ውስጥ ከእያንዳንዱ ወረዳ 25

በጠቅላላው 75 የቆጠራ ቦታዎች በጥናቱ ስለሚሸፈኑ ለዚሁ ጥናት ለተቀጠሩ መረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎች ከነሐሴ 10 እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 1992 ዓ.ም ድረስ ሥልጠና ተሰጥቷል::

ሐ. በዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) የሥልጠና ማዕከል ሁለት የመ/ቤቱ ባለሙያ ጣሊያን ቱሪን በመሄድ አንድ ወር የፈጀ ሥልጠና አግኝተው ተመልሰዋል::

መ. ከአለም አቀፍ የሥራ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ መ/ቤቱ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ጋር በመተባበር በመጋቢት ወር ውስጥ የልጆች የሥራ ሥምሪት ሁኔታ ጥናት አካሂዷል:: ለጥናቱ ሥራ የአሰልጣኞች ስልጠና ለ74 የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከየካቲት 27 ቀን እስከ መጋቢት 4 ቀን 1993 ዓ.ም እንዲሁም በየጽ/ቤቱ የመስክ ሠራተኞች ስልጠና ለ1,447 መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች ከመጋቢት 7 ቀን እስከ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ተካሂዷል::

ሠ. በ1994 ዓ.ም ለሚካሄደው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የአሠልጣኞች ሥልጠና ከሰኔ 5 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሰኔ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ በሁለት የሥልጠና ማዕከላት ተሰጥቷል:: በዚህ ሥልጠና ላይ ከፌዴራል የሚኒስቴር መ/ቤቶች ከክልል ግብርና ቢሮዎችና ከዞን ግብርና መምሪያዎች 33 ባለሙያዎች እንደዚሁም ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ዋናው መ/ቤትና ከቅ/ጽ/ቤቶች የተውጣጡ 503 ባለሙያዎች በስልጠናው ላይ ተሣትፈዋል::

ረ. ከቤተሰብ በጀት ዋጋና የሰው ኃይል ስታቲስቲክስ መምሪያ አንድ ባለሙያ በድህነት ሁኔታ በተመለከተ ለሁለት ሣምንት ቢጋና አክራ ያለም ባንክ ባዘጋጀው ስልጠና ላይ ተሣትፈው ተመልሰዋል::

ሰ. የመ/ቤቱን የባለሙያዎች ብቃት ከፍ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በየተለያየ ወቅት ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል:: ስልጠናውም የሚከተሉትን ያካትታል፣

- በ1992 ስድስት ሠራተኞች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ትምህርት ጀምረው የነበረ ሲሆን፣ ሦስቱ ሲያጠናቅቁ የቀሩት ሦስቱ ደግሞ እየተከታተሉ ናቸው::

- በ1993 የትምህርት ዘመን አራት ሠራተኞች ማለትም አንዱ በዲሞግራፊ ሦስቱ ደግሞ በስታቲስቲክስ የማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም ለመከታተል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተዋል::

- በ1993 ዓ.ም ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በዲሞግራፊ የማስተርስ ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመከታተል በአክራ ጋና ዩኒቨርስቲ በሚገኘው Regional Institute for Population Studies በሚባለው የትምህርት ተቋም በመማር ላይ ይገኛሉ::

- በተለያዩ ጊዜያቶች የድሕረ ምረቃ ፕሮግራም ሊከታተሉ ወደ ቦትስዋና ሄደው የነበሩት አምስት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በበጀት ዓመቱ ትምህርታቸውን አጠናቀው የተመለሱ ሲሆን ሌሎች 6 ደግሞ ከታንዛኒያ ትምህርታቸውን በስታቲስቲክስ መስክ ተከታትለው ሠርተፊኬት በማግኘት ተመልሰዋል::

- በ1993 በጀት ዓመት ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በጀርመንና በጃፓን የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተከታትለው ተመልሰዋል::

ሸ. በ1993 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ያሉትን የቴክኒክና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሥራ ብቃት ከፍ ለማድረግ በነበረው ዕቅድ መሠረት በኢትዮጵያ ሥራ አመራርና በሌሎች የማሰልጠኛ ተቋማት በሚሰጡ የተለያዩ የሙያ ማግደጊያ ሥልጠናዎች ላይ እንዲሣተፉ አድርጓል:: በዚህም መሠረት 22 የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች በሱፐርቫይዘሪ ማኔጅመንት፣ 2 ኦዲተሮች በውስጥ ቁጥጥር፣ 2 ሠራተኞች በዕቃ ግዥና አስተዳደር፣ 19 የቅ/ጽ/ቤት ንብረት ክፍል ሠራተኞች በንብረት አስተዳደር፣ 2 ሠራተኞች በሰው ኃይል አስተዳደር፣ አንድ ባለሙያ በፕሮጀክት ፕላኒንግ፣ ክትትልና ግምገማ፣ 5 ሠራተኞች በቢሮ አያያዝ፣ አንድ ባለሙያ በላይብራሪና በመረጃ አገልግሎት አሠጣጥ ዘዴ እንዲሁም አንድ ሠራተኛ በሪከርድና ማህደር አያያዝ ሙያ ከ5 እስከ 30 ቀናት እንዲሰለጥኑ ተደርጓል::

## 7. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ለ1993 በጀት ዓመት ለአጠቃላይ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል ወጪ ብር 62,328,576 በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 12,035,700 ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 50,292,876 ተፈቅዷል:: ከተፈቀደው በጀት ውስጥ 19.31% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን 80.69% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው:: ሆኖም

በበጀት ዓመቱ ሃብት ሩብ ዓመት ላይ ከተመደበው የካፒታል በጀት ላይ ብር 101,057 / አንድ መቶ አንድ ሺህ ሃምሣ ሰባት ብር / ለግብርና ምርምር ድርጅት በበጀት ዝውውር ተቀንሶ ተሰጥቷል።

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

የተፈቀደው በጀት በሚከተለው የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው። ይኸውም፦

- ለደመወዝ ....................ብር 10,750,400.00
- ለውሎ አበል ................" 41,300.00
- ለሥራ ማስኬጃ ..............." 1,244,000.00 የተያዘ ነው

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው መጠን፦

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው 10,750,400 ብር ውስጥ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 10,355,076.93 ሲሆን ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ከተፈቀደው ብር 10,355,076.93 ( 100% ) ወጪ ተደርጓል።

- ለውሎ አበል ክፍያ ከተፈቀደው ብር 41,300.00 ውስጥ ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 41,300.00 ሲሆን ከተፈቀደው ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 37,750.19 (91.40% ) ይሆናል።

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው 1,244,000 ብር ውስጥ ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 1,111,431.27 ሲሆን ከተፈቀደው ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 1,091,134.97 ( 87.7% ) ነው።

ለ1993 በጀት ዓመት ውስጥ ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1992 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ለመደበኛ በጀት በእጅ ገቢ የሆነው ብር11,507,808.20 ሲሆን ወጪ የሆነው ብር 11,483,962.09 ነው። አፈፃፀሙ በእጅ ከገባው የገንዘብ መጠን ጋር ሲነፃፀር 99.8 ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 95.4 በመቶ ይሆናል።

### ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1993 ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮግራሞች ብር 50,191,729.00 የተፈቀደ ሲሆን ይህም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር

23,121,151.00፣ ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናት ፕሮግራም ደግሞ ብር 27,070,668 የተፈቀደ ነው።

ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተፈቀደው በጀት ብር 21,866,742.31 ( 94.6% )ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናትና የዝግጅት ሥራዎች ደግሞ ከተፈቀደው በጀት ብር 26,276,348.00 (97.1% ) ወጪ ሆኖ በሥራ ላይ ውሏል። ለሁለቱ ፕሮግራሞች ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በጠቅላላ ወጪ የሆነው ብር 48,143,090.31 ( 95.9% ) ነው።

ለ1993 በጀት ዓመት ከተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል በጀት ብር 60,441,190.51 ተጠይቆ በእጅ የገባ ሲሆን ብር 59,627,052.40 ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ወጪ የተደረገው በእጅ ከገባው የገንዘብ መጠን ጋር ሲነፃፀርም 98.6 በመቶ ይሆናል። አሃዛዊ መረጃውም በሠንጠረዥ 4 ላይ ተመልክቷል።

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ1993 ዓ.ም በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 4

| ተራ ቁጥር | የበጀት አጠቃቀም | ለ1993 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት /በ03 እና በ04/ |
|---|---|---|---|---|---|
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 1 | ለመደበኛ በጀት | 12,035,700.00 | 11,507,808.20 | 11,483,962.09 | 23,846.11 |
| 1.1 | ለደመወዝ | 10,750,400.00 | 10,355,076.93 | 10,355,076.93 | - |
| 1.2 | ለውሎ አበል | 41,300.00 | 41,300.00 | 37,750.19 | 3,549.81 |
| 1.3 | ለሥራ ማስኬጃ | 1,244,000.00 | 1,111,431.27 | 1,091,134.97 | 20,290.30 |
| 2 | ለካፒታል በጀት | 50,191,819.00 | 48,933,382.31 | 48,143,090.31 | 790,292.00 |
| 2.1 | ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም | 23,121,151.00 | 21,862,939.31 | 21,866,742.31 | /3,803.00/ |
| | 8202 | 130,000.00 | 130,000.00 | 107,100 | 22,900.00 |
| | 8301 | 7,678,212.00 | 6,419,939.31 | 6,419.939.00 | - |
| | 8302 | 1,802,770.00 | 1,802,800.00 | 1,212,907.00 | 589,893.00 |
| | 8303 | 12,554,009.00 | 12,534,000.00 | 13,157,000.00 | /603,000/ |
| | 8304 | 956,160.00 | 956,200.00 | 969,796.00 | /13,596/ |
| 2.2 | ለግብርና ቆጠራ የሙከራ ጥናትና ሌሎች የዝግጅት ተግባራት | 27,070,668.00 | 27,070,443.00 | 26,276,348.00 | 794,095.00 |
| | 8205 | 5,949,682.00 | 5,949,595.00 | 5,949,595.00 | - |
| | 8301 | 157,230.00 | 157,200.00 | 198,800.00 | /41,600.00/ |
| | 8302 | 37,632.00 | 37,600.00 | 30,200.00 | 7,400.00 |
| | 8303 | 13,610,019.00 | 13,609,943.00 | 12,781,648.00 | 828,295.00 |
| | 8305 | 7,316,105.00 | 7,316,105.00 | 7,316,105.00 | - |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **62,227,519.00** | **60,441,190.51** | **59,627,052.40** | **814,138.11** |

## 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መ/ቤት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመቱ ለሚካሄዱት ጥናቶች እገዛ የሚያደርጉ ሥራዎች ተከናውነዋል። እነዚህም፦

8.1 <u>የዕቃ ግዥን በተመለከተ</u>

ከሐምሌ 1 ቀን 1992 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት እንዲውሉ ብር 8,804,591.50 ወጪ ተደርጎ የተለያዩ ቋሚ፣ አላቂ ዕቃዎችና የአገልግሎቶች ግዢ የተፈፀመ ሲሆን፣ በ1992 ተጠይቶ የነበረው የግብርና ቆጠራ መገልገያ ዕቃዎች (ጂንጥላ፣ ኮምፓስና ሜትር) ግዢ በጀቱ የተፈቀደው በ1993 ዓ.ም በመሆኑ በብር 5,348,480 የዕቃዎቹ ግዢ ተፈፅሟል፡፡ ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንረጠዥ ቀርቧል፡፡

<u>በ1993 በጀት ዓመት የተፈፀመ የዕቃና የአገልግሎት ግዥ</u>

<u>ሠንጠረዥ 5</u>

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | የገንዘብ መጠን | |
|---|---|---|---|
| 1 | የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች | 2,284,416 | 71 |
| 2 | የጽሕፈት መሣሪያና የማተሚያ ዕቃዎች | 1,587,291 | 34 |
| 3 | የቢሮ ዕቃዎችና ሌሎች የመገልገያ ዕቃዎች | 322,171 | 92 |
| 4 | ለሕንፃ ጥገናና የጥገና ዕቃዎች | 116,767 | 95 |
| 5 | ነዳጅና ቅባት | 2,397,016 | 84 |
| 6 | ጃንጥላ፣ ኮምፓስና ሜትር | 5,348,480 | 00 |
| 7 | ለግብርና ቆጠራ ተጨማሪ ዕቃዎች | 1,832,250 | 24 |
| 8 | ሌሎች ወጪዎች | 264,176 | 69 |
| | ድምር | 14,153,071 | 50 |

8.2 <u>ትራንስፖርትና ጥገና</u>

- ለ159 መኪናዎች ከአንድ እስከ ሦስት ጊዜ ድግግሞሽ ከባድና መለስተኛ ጥገናዎች እንዲሁም ሰርቪስ በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች አማካይነት ተደርጎላቸዋል፡፡ ለዚህም ብር 4,110,218.49 ወጪ ሆኗል፡፡

- 20 መኪናዎች በመድን ድርጅት አማካይነት እንደጉዳታቸው መጠን አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው ለአገልግሎት ብቁ ሆነዋል፡፡ አንድ መኪና በደረሰበት ከባድ የመገልበጥ አደጋ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ ዋጋው ተከፍሎ ኢንሹራንስ እንዲረከበው ተደርጓል፡፡

- 10 የመ/ቤቱ መኪናዎች ለምርጫ ቦርድ፣ አደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኮሚሽን እንዲሁም ለመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በትውስት ተሰጥተው ለሁለት ወራት አገልግሎት ሰጥተዋል።

- ለበጀት ዓመቱ የመ/ቤቱን ተሽከርካሪዎች ለመጠገን አምስት ጋራዦች የሰርቪስ ኮንትራት የተፈራረሙ ሲሆኑ የመ/ቤቱ የመስክና የሰርቪስ መኪኖች በሙሉ ለአንድ ዓመት የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል።

- በእርጅና ምክንያት አገልግሎት ሊሰጡ ያልቻሉ 5 /አምስት/ መኪናዎች በፋይናንስ አዋጅና ደንብ መሠረት በጨረታ እንዲሸጡ ተደርጎ በብር 275,900.00 /ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር/ የተሸጡ ሲሆኑ ብዙ ቢሮዎችና መጋዘኖች አጣበው የነበሩ የተለወጡና አሮጌ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች በብር 27,000 / ሃያ ሰባት ሺህ ብር / ተሸጠው ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል።

8.3. <u>የሕትመት ዋና ክፍል</u>

በ1993 በጀት ዓመት በሕትመት ዋና ክፍል አማካይነት 252,249 ጥራዞችና እንዲሁም በብትን 15,692,101 ገጾች እንዲታተሙ በማድረግ ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ እንዲቀርቡ አድርጓል። በተጨማሪም ከመ/ቤቱ መምሪያዎችና አገልግሎቶች የሚቀርቡ የፎቶ ኮፒና የሚባዙ ፅሑፎችን እንደ ጥያቄአቸው ምላሽ ሰጥቷል።

8.4 <u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

ሀ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የማኔጅመንት አባላት፣ ከልዩ ልዩ መምሪያዎችና አገልግሎቶች የተውጣጡ ባለሙያዎችና የሃያ ሁለቱም ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች በተገኙበት ከሐምሌ 26-27 ቀን 1992 ዓ.ም በግዮን ሆቴል አዳራሽ ስብሰባ ተካሂዷል። በስብሰባው ላይ በ1992 በጀት ዓመት ስለተካሄዱ ጥናቶች፣ በአሠራር ላይ ስለታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችና ስለአጋጠሙ ችግሮች፣ ለችግሮቹ ስለተሰጡ የመፍትሄ ሃሣቦች እንደዚሁም በ1993 ዓ.ም መ/ቤቱ በሚያካሂዳቸው የተለያዩ ጥናቶች የመረጃ ጥራትን ለማሻሻልና የጥናቶቹን ውጤት በወቅቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ለማድረግ በሚያስችሉ ሁኔታዎች ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል።

ለ. የጥናት መረጃዎችን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል ተብሎ ከሚታመንበት ስታቲስቲካዊ ቴክኒክ አንዱ የጥናት ቦታዎችን /ቤተሰቦችን /ድርጅቶችን በማቀያየር መረጃ

መሰብሰብ ነው፡፡ ሆኖም ዘዴው ተጨማሪ የፋይናንስና የጊዜ ወጪን ስለሚጠይቅ በምትኩ የመስክ ሠራተኞችን ምድብ ቦታ በማቀያየር ጥናቱን ማካሄድ እንደአማራጭ ይሰራበታል፡፡ በመሆኑም በ1993 ዓ.ም የጥናት ዓመት የሁሉንም መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች የቀድሞ ምድብ ቦታ በማቀያየር እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

ሐ. በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ ወይም ጥራታቸውን ያልጠበቁ የመስክ መገልገያ መሣሪያዎችና ዶክሜንቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚያቀርቡት መጠየቂያ መሠረት ወጪ ሆነው እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡

መ. ለግብርና ናሙና ቆጠራ ዝግጅት እንዲረዳ በናሙና በተመረጡ 51 ወረዳዎች ከእያንዳንዱ ወረዳ ሁለት የቆጠራ ቦታዎች ድጋሚ የማካለልና ከቀድሞው ቆጠራ ቦታ ካርታ ጋር የማመሳከር እንዲሁም ጥራቱን የመፈተሽ ተግባር ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም አሁን ያለውን የመስተዳደር ክልሎች የወሰን አከላለልና ስያሜ ከቀድሞው ጋር በማገናዘብ መረጃው በቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ተሰብስቦ ወቅታዊ ተደርጓል፡፡

ሠ. ከግል ገበሬ ይዞታ ውጪ የሆኑትን ሌሎች እርሻዎች በግብርና ናሙና ቆጠራው ለመሸፈንና የእርሻዎቹን ዝርዝር ወቅታዊ ለማድረግ እንዲቻል በተዘጋጁ መጠይቆች መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ ወቅታዊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ረ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለ17 የተለያዩ መ/ቤቶች በቀረበለት የካርታ ሽያጭ ጥያቄ መሠረት የ51 ወረዳ ካርታዎችን በብር 1,836 (አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር) ኮፒ ተደርጎ ተሸጦላቸዋል፡፡

ሰ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከሚያካሂዳቸው ጥናቶች የሚዘጋጁ ሪፓርቶችን ለተጠቃሚዎች በነፃና በሽያጭ የሚያሰራጭ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 11,131 ሪፓርቶችን ለሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ለመንግሥትና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ለግለሰቦች አሰራጭቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 7,750 ሪፖርቶች በነፃ የታደሉ ሲሆን ቀሪዎቹ 3,381 ሪፖርቶች ደግሞ በብር 78,518.05 ( ሰባ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አሥራ ስምንት ብር ከዜሮ አምስት ሣንቲም ) በሽያጭ ተሰራጭተዋል፡፡

ሸ. የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራን ለማስፈፀም እንዲቻል የኢፌዲሪ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 238/93 ማውጣቱ ይታወሣል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 እና 5 መሠረት የቆጠራውን ተግባር የሚያስፈፅም ኮሚሽን ከማዕከል ጀምሮ በየደረጃው እስከ ወረዳ ድረስ እንዲቋቋም የሚያዝ መሆኑን የማዕከል ኮሚሽኑ ግንቦት 30 ቀን 1993 ዓ.ም

የተቋቋመ ሲሆን የክልልና የዞን ኮሚሽኖች ደግሞ ከሰኔ 10 ጀምሮ በመላው አገሪቱ እንዲቋቋሙ ተደርጓል።

ቀ. በ1994 ለሚካሄደው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራን ተግባር ለማስፈጸም አገልግሎት የሚውሉ ተጨማሪ ጽ/ቤቶችን መክፈት በማስፈለጉ ቀድሞ ከነበሩት 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በተጨማሪ ሌሎች 25 ጽ/ቤቶችን በአገሪቱ ባሉ ዞኖች በመክፈት የቆጠራውን ተግባር በ47 ጽ/ቤቶች ለማስተባበርና ለመስራት ታቅዷል። ለእነዚህ አዲስ ለተከፈቱ ጽ/ቤቶችም አስፈላጊው የሰው ኃይልና የቢሮ ቁሣቁሶች እንዲሟሉላቸው እየተደረገ ይገኛል።

በ. የመ/ቤቱ መዋቅር ሲፈቀድ አስፈላጊው የሰው ኃይል አሟልቶ ካለመያዙ ሌላ የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን በየጊዜ እየሰፋ በመሄዱ የተጓደለውንና አዲስ ተጨማሪ የሰው ኃይል ተሟልቶ እንዲቀጠር ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ጥያቄ ቀርቦ ከተጠየቀው 734 የሰው ኃይል ውስጥ የ191 የሥራ መደብ ተፈቅዶ ስለመጣ ለዚሁ የሚሆን የሥራ ዝርዝር በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።

## 9. <u>በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች</u>

ሀ. የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገጽታዎች የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ሰብስቦና አጠናቅሮ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በወቅቱ የማቅረቡ ተግባር የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት ነው። ይህንን መወጣት ይቻል ዘንድ በየዘርፉ የሰለጠነና ልምድ ያካበተ ባለሙያ መኖር ያስፈልጋል። ነገር ግን የመ/ቤቱ ነባርና የሰለጠኑ ሠራተኞች ለተሻለ ደመወዝ ወደሌላ መ/ቤት እንዳይሄዱ ለማቆየትና በተለያየ ምክንያቶች ማለትም በሞት፣ በጡረታ... ወዘተ በተለዩት ምትክ ተጨማሪ አዳዲስ ባለሙያዎች ከገበያ ፈልጎ ለመቅጠር እንዲቻል ለመ/ቤቱ ልዩ የደመወዝ ምደባ ስኬል እንዲፈቀድና ተግባራዊ እንዲሆን ያስፈልጋል። በተለይም በ1994 አገር አቀፍ የግብርና ቆጠራን ለማስፈፀም መ/ቤቱ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማቆየት ጥረት ቢያደርግም ችግሩ ከአቅም በላይ እየሆነ መጥቷል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ 13 ባለሙያዎች መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን የቆጠራውን ሥራና ሌሎች የተጀመሩ ጥናቶችንና ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም የምንቸገር መሆኑን እንገልጻለን።

ለ. መ/ቤቱ በተለያየ ዘርፍ ለሚያካሂዳቸው ጥናቶች እገዛ እንዲያደርጉ ከውጭ አገር በእርዳታ የተገኙ የፋክስ ማሽኖች አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ከቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ ተጠይቆ እስከ አሁን አዋንታዊ ምላሽ አልተገኘም። እርዳታ ሰጪው

ድርጅት ማሽኖቹ ለሥራ አስፈላጊነታቸውን አምኖበት የሰጠ በመሆኑና ዋናው መ/ቤት ከቅ/ጽ/ቤቶች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት ከማቃለሉም በላይ የሚያካሂደውን ሥራ ለማቀላጠፍና ለወቅታዊ መረጃ ልውውጥ ስለሚረዱ ለጥናቶቹ ጥራት መሻሻል አስተዋጽዖ ይኖረዋል:: በመሆኑም የተጠየቁትን የፋክስ ማሽኖች እንደገና ትኩረት በመስጠት ፈቃድ ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የሚያደርግበትን መንገድ ሊመቻች ይገባል::

ሐ. እያደገ የመጣው የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች የሚቀጠሩ ሲሆን ከዚህ በፊትም የተቀጠሩት ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት ከመ/ቤቱ አቅም በላይ እየሆነ መጥቷል:: ይህም በመሆኑ በርካታ የሥራ ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶቻቸው ተራርቀው የሚሰሩበት እንዲሁም አንድ ክፍል ከአቅም በላይ የሆኑ የሰው ብዛት እንዲይዝ በማድረጋችን ቢሮዎቻችን ለሠራተኞች የተመቻቹ የሥራ ቦታ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የሥራ ተነሣሽነት እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል:: እንደዚሁም በ1994 ዓ.ም በሚካሄደው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ ምክንያት ተጨማሪ የሰው ኃይልና የሎጅስቲክስ አቅም መ/ቤቱ እንደሚያገኝ የሚጠበቅ በመሆኑ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እንድንችል ከመንግሥት ድጋፍ እንፈልጋለን::

መ. በአዲሱ የፋይናንስ አዋጅና ደንብ መሠረት አንዳንድ አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦች በተለይ የማተሚያ ጥገና የሚሰጡ ግለሰቦች በየአመቱ የገንዘብ ሚ/ር በሚያወጣው የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የመጠገን ችሎታ እንደሌላቸው ለመገንዘብ ተችሏል:: በመሆኑም መ/ቤቱ በአገልግሎት ብዛትና በእርጅና ምክንያት ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የማተሚያ መሣሪያዎች ለማስጠገን ችግር እያጋጠመው ይገኛል:: ስለዚህ ይህንንና ሌሎችንም ተመሣሣይ አገልግሎት ለሚሰጡ ግለሰቦች የተለየ የአፈፃፀም መመሪያ በሚመለከተው ክፍል ቀርቦ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ እንዲመቻች እንጠይቃለን::

ሠ. መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ጥናቶች በየጊዜው የሚገዙ ተሽከርካሪዎች በአስመጪ ኩባንያዎች በኩል በቂ መለዋወጫ ስለማይቀርብ የጥገና ወጪያቸው ከሚጠበቀው በላይ በየዓመቱ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ በ1994 በጀት ዓመት ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ብቁ ሆነው እንዲገኙ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ተመሣሣይ የጥገና ሥራ እንዲካሄድ ተደርጎ ነበር:: ሆኖም የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች በቂ መለዋወጫ ባለመኖሩና ያለውም መ/ቤቱ ከሚጠብቀው በላይ ዋጋው ውድ በመሆኑ ለጥገና ከታሰበው ጊዜ በላይ ተሽከርካሪዎቹ ያለሥራ ቆመዋል፣

አሁንም ቆመው ይገኛሉ። ስለዚህ ለመ/ቤቱ ሥራ ብቁ ሆነውና በቂ መለዋወጫ የሚገኝላቸው ተሽከርካሪዎች ለወደፊቱ የሚገዙበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል።

ረ. በ1994 ለሚካሄደው የግብርና ቆጠራ የባለሥልጣኑ መ/ቤት 15,000 በላይ ተጨማሪ የሰው ኃይል ቅጥር የሚካሄድ ሲሆን፣ እነዚህ ሠራተኞችን በሥራው ላይ ለማሠማራት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ ስልጠና ይካሄዳል። ሆኖም በአንዳንድ ክልሎች 12ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ተቀጣሪዎች በብር 285 ደመወዝ ተከፍሏቸው ለመሥራት ፈቃደኞች ሆነው ባለመገኘታቸው ከአጎራባች ክልሎች ለመመልመል ተገደናል። ይህ አሠራርም በተለይ ለመረጃ መሰብሰብ ተግባር የማያቀጣና የማያዛልቅ ስለሚሆን አጭር ጊዜ / አንድ ዓመት ድረስ / የሚወስድ ጥናት የመረጃ ሰብሳቢዎች በኮንትራት የቅጥር መነሻ ደመወዝ የሚሻሻልበት መንገድ እንዲመቻች እንጠይቃለን ።